እናት አገር ትጣራለች

ከወንድሙ መኮንን

"አዳራሹ ቤቴ ችምችምቱ በከሴ
እኔን የሚገርመኝ፣ እያደርኩ ማነሴ።"

እናት ኢትዮጵያ ሰፊ መሬትና ብዙ ሕዝብ ነበሯት። ይኸን ለማረጋገጥ በቅርብ ጊዜ ከኑቢያ አለቶች ተፈልፍለው በድንገት ተገኝተው፣ በመሪ ራስ አማን በላይ የተተረጎሙትን ጽሑፎች ብቻ ማንበብና፣ አስፈላጊም ከሆነ ከአረቦችና ከግሪኮች ጽሕፋዊ መረጃዎች ማመሳከር ይቻላል። በትንሹ፣ ከዛሬዩት ኢትዮጵያ መቶ ጊዜ ትሰፋ ነበር ብንል ማጋነን አይሆንም። ጠላቶች በየጊዜው እየተነሱባት፣ ሲሸረሸሯት፣ ሲቆርሷት፣ ሲያሳንሷት፣ አገሪቷ ያጣቻቸው ግዛቶች ኢትዮጵያ መሆናቸው ሲቀር፣ ሕዝቦቿም ኢትዮጵያዊነታቸው እንዳልነበረ እየሆኑ ሄደዋል። እናት ኢትዮጵያ ስትቆረስ፣ ስትቦጨቅ፣ ስትዘረፍ፣ አላልቅ ብላ እነሆ ዛሬ ኩርማን አከላለች።

የኢትዮጵያን ስም ከምድር ገጽ ለመደምሰስ ለብዙ ሺ ዓመታት ሲታገሉ የነበሩ የውጪ ጠላቶች ቢሏት፣ ቢወሯት፣ ቢወጉአት፣ ቢቆርጡአት፣ ቢቦጭቋት ስሟ የተብረድከ ስም ነው ናውና ስልሟ፣ ለክብሯ፣ ስትመከትና ስታስቸገረቸው ኑራ፣ ዛሬ በለስ ቀንቶአቸው ዘዴውን፣ ብልሀቱን በስተመጨረሻ ያገኙ ይመስላል። በፊት ኢትዮጵያ ስትወረር፣ ወራሪውን ኃይል ለይቶ አውቆ ተጠራርቶ መመከት ልማድ ስለሆነ፣ ከ3000 ዓመታት በላይ ስሟን ለመጠሪያ ለማስከበር ተችሎ ነበር። ጠላቶቿ አሁን ያገኙት ዘዴ ግን ከምንጊዜውም የከፋና አደገኛ ነው። ያገሩን ሠርዶ በአገሩ በሬ እያረሱት ነው። ኢትዮጵያዊ አጥፊ መሣሪያ ተገኝቷል።

አረሱት! አረሱት፣ አሉኝ የሁመራን መሬት
የመተማን መሬት፣ የአርማጭሆን መሬት
አረሱት፣ አረሱት፣ የጎንደርን መረት
አርሱት! አረሱት፣ የኢትዮጵያን መሬት
አርሱት! አርሱት፣ ያውም የኛን ዕጣ
እንሱ ምን ያርጉ፣ ከኛ ሰው ሲታጣ (ፋሲል ደሞዝ)

ከዚያችው ይዛ ከቀረችው ኩርማን መሬት፣ ዓይናችን እያየ፣ ከአገር በበቀሉት ከሀዲዎች አየቆረጡአት፣ እየቦጨቁአት፣ እያሳነሷት ነው። እንዚህ እራሳቸውን ለውጭ ጠላቶች በቅጥረኝነት ያጩት አርሞች፣ በፔትሮ ዶላር ድጋፍ ተዋግተው፣ ደም ከፍለው ኤርትራ የምትባል አገር ከኢትዮጵያ ጉያ ተፈልቅቃ በሀይል ወጥታ አገር ሁና እንድትታወቅ አደረጉ። ኢትዮጵያ ከአብርኳ በወጡት የናት ጡት ነካሽ አመኬላዎች ደማች፣ ተቦጨቀች፣ ተቆረሰች። ኢትዮጵያ አነሰች። የተገንጠለችው አካል ውስጥ የቀሩትም ኢትዮጵያውያን ለብዙ ሺህ ዓመታት የታወቁበትን ኢትዮጵያዊነት መታወቂትያቸውን ቅዳደው እንደቆሻሻ ልብስ ወርውረው ጥለው አዲስ ሕዝብ፣ "ኤርትራውያን" ተባሉ። ዛሬም "እምብዬው! አሻፈረኝ፣ ኢትዮጵያዊነቴን አልቃትም" ያሉት ወገኖቻችን እየታደኑ ተጨፈጨፉ። የግድ፣ ኦሮሞ ነኝ፣ አማራ ነኝ፣ ትግሬ ነኝ፣ ወላይታ ነኝ፣ ኣሧከ ነኝ፣ ኑዌር ነኝ ... በል" ተብለው ኢትዮጵያዊነትን ተፍተው እንዲጥሏት ተገደዱ። በዘር እየለዩም፣ እራሳቸውን የኢትዮጵያ መንግሥት አሰኝተው፣ አሧኩ ላይ፣ አማራው ላይ፣ ኦሮሞው ላይ፣ መዝንግሩ ላይ፣ በተቀነባበረ ሁኔታ የዘር ማጥፋት ወንጀል አፋፋሙ። ያንን ሁሉ ያደረጉት፣ ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያዊነታቸውን ኢንዲጠሉ በኢትዮጵያ "መንግሥት" ስም ነበር። ኢትዮጵያዊነት የቁም- ስቅል ስቃይ የሚያበላ አሳር ሆነ። መቻል ያቃተን በአገነኘው ኬላ አሳብረን ወደ ውጭ በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ እንድጎርፍ ሚሊዮን በሚሊዮን የምንቆጠር ጎርፈን ተሰደድን። ውጪ የተዋለድን ስድተኞች ልጆቻችን እንዳሉ ኢትዮጵያውያን ሳይሆኑ የተወለዱብት አገር ዜጎች ናቸው። እኛም ለመኖር ብለን ኢትዮጵያዊ ፓስፖርታችንን አስረክበን የውጭ አገር ፓስፖርት

ጨበጥን። ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ሕጋችን የሌላ አገር ፓስፖርት ስንይዝ፣ ኢትዮጵያዊነታችን ይሰረዛል። በሕግ መሠረት ኢትዮጵያዊያን ሳንሆን አሜሪካውያን፣ እንግሊዛውያን፣ ጀርማናውያን ... ሁነናል።

ፓስፖርታችን ቢለወጥ ኢትዮጵያዊነታችን በውስጣችን ተቀብሮ አይለውጥም። እኛስ ለሀገራችን በስደትም ሆነን እንታገልላታለን። የሚያሳስበው በዚህ ሁኔታ ከቀጥለ ኢትዮጵያ የምትባልስ አገር ልትኖረን ትችላለች ወይ? ነገሩ አሳሳቢ ነው። "ወያኔ" በመባል የሚታወቀው ቅጥረኛ፣ አንድ አገር ሊወጣው የሚችል መሬት ቆርጦ ለሱዳን አስረከቧል። የቴውድሮስ የትውልድ ስፍራ ከጎንደር ተወስዶ ሱዳን ሁኗል። "ጎንደር ሱዳን ገብታ ሆነችን ጎርቤት" ተብሎ የተዘፈነው ለዚህ ነው። የወሊጋ ምደር ሱዳን ገብቶላችሁአል። ጋምቤላ ለሱዳን በስጦታ መልክ ተሰጥቷል። በደሉ በዚህ አላከተመም። መሀል አገር ያለው ለም መሬት እየተሸነሸነ ለዐረብ ቱጃሮች በርካሽ እየተቸበቸበ ነው። ኢትዮጵያን ከዳር ሳይሆን ከመሀል ልቧን እየቦጠረቋት ነው። ወገን! እናት አገር፣ "ሎጀቼ ድረሱልኝ" እያለች ትጣራለች። ጆሮ ያለው ይስማ። ኧረ እንረባረብ!

ወንድማችን ኦባንግ ሜቶ ባለፈው ጊዜ በስልክ፣ ምርር ብሎት ሲያነጋግረኝ፣ "ወንድሙ! አገራችን ልትጠፋ ነው! ወያኔ አገራችንን ሊያጠፋ ተነስቷን። እርስ-በርሳችን ከማናከስ አልፎ፣ አገራችንን ደብዛዋን ሊያጠፋት ነው። ተሳክቶለት ኢትዮጵያን ቢያጠፋት፣ እስቲ ኢግዚአብሔር ያሳይህ! ሰዎች ሲጠቁኝ 'ከየት መጣሁ' እላለሁ" ብሎ እምባዬን አመጣሁ።

ኦባንግ ወንድማችን ነጋ ጠባ ድፋ ቀና የሚለው ይኸው አሳስቦት ነው። ኢትዮጵያውን ለማዳን መላእክት እንደድሮው በከንፋቸው ከላይ እየከንፉ አይመጡም። "እንድረዳችሁ እርዱኝ ይላል እግዚአብሔር" የሚባል አባባል አለ። እኛ እራሳችንን ስንረዳ ነው እግዚአብሔርም ሊርዳን የምነሳው። ለኢትዮጵያ ያለናት እኛው ልጆቸዋ ነን። ሎንዶን ያሉ የተወሰኑ ኢትዮጵያዊያን የኦባንግ ሜቶን መልዕክት ሰምተው ቲኬት ገዝተው መስከረም 3 ቀን (September 13) ዋሽንግተን ላይ በሚደረገው ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ ላይ ለመገኘት ዝግጅት ላይ ናቸው። ከሌሎችም የአውሮፓ አገሮች፣ ዋሽንግተን ለመሄድ እንዲሁ የተነሱ ወንድሞችና እህቶች እንደተዘጋጁ ሰምተናል። የኢትዮጵያ ልጆች ከአውሮፓ ወደ ዋሽንገትን ለጉዞ ዝግጅት ሲያደርጉ አሜሪካ ያላችሁስ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ጥሪው ደርሶአችኋል? ሰምታችሁአል? ለኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆቿ ለመሆን ታጥቃችሁ ተንስታችሁአል? እምዬ ኢትዮጵያ ትጣራልች! ኑ ድርሱልኝ ትላለች። እስቲ አንድ ቀን ወጥተን እንጨህላት። አማራ አማራ አንበል! ትግሬ ትግሬ አንበል! ኦሮሞ ኦርሞ አንበል። ኢትዮጵያ ነጻ እስክትወጣ ድርስ ሁላችንም ነጻነት አይኖረንም። አንድ ላይ እንነሳ!

ፕሬዝደንት ኦባማ ጥሩ ሰው ናቸው ሲባል እንሰማለን። ኢትዮጵያንም ይወዱኢታል የሚል ጭምጭምታ እንሰማለን። አንድ ነገር ግን አንርሳ። ሺህ ጊዜ ቢወዱን እኛ የኢትዮጵያ ልጆች አንድ ላይ ተነስተን በአንድ ቀን ለኢትዮጵያ ካልጮህን አይስሙንም። ከመጤፍም አይቆጥሩንም። አንድነታችን ኃይላችን ነው።

በሚቀጥለው ሎንዶን ውስጥ በተደረገው በኦባንግ ሜቶ ንግግር የዛሬውን መልዕክቴን አበቃለሁ።

> "እኔ ስወለድ፣ ብሔር አልነበረኝም! እኔ ስወለድ ቋንቋ አልነበረኝም! አንድ ነገር ግን በዕርግጠኝነት መናገር እችላለሁ። ሰው ነበርኩ።
>
>
>
> አኟኩም ነህ የተባልኩት በደንብ መናገር ከቻልኩ በኋል ነው። የአኛኩም ቋንቋ መናገር የተማርኩት ከተወልድኩ በኋላ ነበር። ባሕሉንም ወጉንም የተማርኩት ከተወልድኩ በኋላ ነበር። በአጋጣሚ ጋምቤላ ሳይሆን ትግራይ ተወልጄ ቢሆን ኑሮ ታሪኬ ሌላ በሁነ ነበር። ልብ በሉ! እኔ ከአኟኩነቴ በፊት ሰው ነበርኩ። አሁንም ሰው ነኝ። ወደፊትም ሰው ነኝ። ከዘሬ በፊት ሰውነቴ ይቀድማል። እንዲህ እንዲህ እያለ ነው ወደ ትንሹ የሰውነቴ ክፍፍል ተራ በተራ ሁሉም የሚመጣው። እኔ ኦባንግ ሜቶ ኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠርኩ ሰው ነኝ። ጋምቤላ ኢትዮጵያ ውስጥ ናታ! አኟኩ ቤተሰቦቼ ደግሞ ጋምቤላ ውስጥ ናቸው። ያ የጋምቤላ ልጅ ያደርገኛል። ከዚያም ከአኟኩ ቤተሰብ የተገኘሁ በመሆነ አኟኩ ነኝ። ስለዚህ ለኔ ከዘሬ በፊት ሰውነቴ ይቀድማል።

እያንዳንዳችሁን ትክ ብዬ ሳይ፣ ዘራችሁን መናገር አልችልም። ምን እንደሆናችሁ አላውቅም። ደግሞም ማወቅ የለብኝም። ሁለት ነገሮችን ግን በግልጽ ልነጋርችሁ እችላለሁ። ሁላችሁም የሰው ልጆች ናችሁ። ያ ወንድሞቼ ያደርጋችሁአል። ቀጥሎ ሁሉችሁም ወደዳችሁም ጠላችሁም ኢትዮጵያውያን ናችሁ። አይደለሁም የምትል ሰው ካለህ ይኸ ስብስብ የኢትዮጵያውያን ስብሰባ ነውና እዚህ ምን ታደርጋለህ?

አገራችን ኢትዮጵያ ከፍተኛ አደጋ ላይ ናት። በአሁን ሰዓት የሚያስተዳድራት ኃይል ሊያለማት ሳይሆን ሊያጠፋት የተነሳ አዙሪ መሰሪ ነው። አገራችን የምንላት ኢትዮጵያ ከመጥፋቷ በፊት ኢትዮጵያውያንን በአንድ ላይ ተነስተን እጅ-ለጅ ተያይዘን እናትርፋት!"

እንግዲህ መስከረም 3 ቀን (September 13) ዋሽንግተን በሚደረገው ሥር-ነቀል ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ሁላችሁም ባንድነት ወጥታችሁ ታሪክ ሥሩ። የኢትዮጵያ የበላይ ጠባቂ የሆነው ቸር አባት ጌት ይርዳን።

እግዚአብሐር - ቸር አባት ጌታ!
እሱ ራሱ ይርዳን! አገራችንን ይታደጋት! አሜን